
# ቻንድራስ ማጂክ ላይት (Chandra's Magic Light)




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

**ጭብጦች (Themes)፤** ቤተሰብ፤ ብርሃን፤ ጽናት (Perseverance)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** ቻንድራ (Chandra) የጸሃይ መብራት(solar lamp) የቤተሰቦቿን ቤት በሂማላያስ (Himalayas) ከፍታ ላይ እንደሚያበራ እና ወንድሟ በምሽት በቀላሉ እንዲተነፍስ እንደሚረዳው ታውቃለች። ነገር ግን አንድ ለመግዛት በቂ ገንዘብ እንዴት ለማግኘት ትችላለች?

**ደራሲ፤**
ቴሬሳ ሃይን
(Theresa Heine)

**ሰዓሊ (Illustrator):**
ጁዲ ጉየፊር
(Judith Gueyfier)

## የንባብ ጊዜ!



**ከንባብ በፊት፤** የታሪኩን ርዕስ ያንብቡ እና ሽፋኑን ይመልከቱ። ልጅዎን በታሪኩ ውስጥ ምን ይከሰታል ብለው እንደሚያስቡ ይጠይቁት።

**በንባብ ጊዜ፤** በሚያነቡበት ወቅት፣ "ቻንድራ ምን እየሰራች ነው? ለምን እንዲህ ታደርጋለች?" ብለው ይጠይቁ።

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ፤**

- ቻንድራ የአስማት ብርሃን እንዴት አገኘች?
- አስማታዊ ብርሃን እንዴት እንደሚሰራ ያብራሩ።
- በታሪኩ መጨረሻ ላይ ምን ሆነ?

## ሆን ተብሎ የሚደረግ ንግግር (INTENTIONAL TALK)


**ከጽሑፉ ባሻገር ማሰብ (Thinking Beyond The Text)-** ለአዳዲስ አንባቢዎች ማዳበር የሚገባቸው ጠቃሚ ክህሎት በሚያነቡት እና በዙሪያቸው ባለው ዓለም መካከል ግንኙነት መፍጠር ነው። በዚህ መንገድ የራሳቸውን ሃሳብ ወደሚያነቡት ነገር አምጥተው ስለ አንድ ታሪክ ወይም ጽሑፍ የበለጠ ግንዛቤን ያዳብራሉ። እንዲሁም ሃሳባቸውን እና አመለካከታቸውውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይረዳቸዋል። ቻንድራስ ማጂክ ላይትን (Chandra's Magic Light), እያነበቡ

ልጅዎን ስለ ቤተሰብዎ የሚያስታውሳቸውን የታሪኩን ክፍል፣ ወይም ይህን መጽሐፍ ከማንበባቸው በፊት ያዩዋቸውን ነገሮች ሳይቀር እንዲያገኙ ያበረታቱት። "የቤተሰባችን አባላትን ለመርዳት ምን አይነት ነገሮች እናደርጋለን?" ብለው ይጠይቁ። ይህም ግንኙነቶችን እንዲፈጥሩ እና መጽሐፉ እንዴት ከዓለማቸው ጋር እንደሚስማማ እንዲመለከቱ እና ከታሪኩ ጋር ትርጉም እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል።

## ተዛማጅ ተግባራት

**በፀሐይ ኃይል የሚሠራ የውሃ ማሞቂያ ሙከራ** (Solar-Powered Water Heating Experiment)
ቁሳቁሶች፤ 2 ትናንሽ ንጹህ ወይም ነጭ ብርጭቆዎች፤ የሞቀ ውሃ፤ ጥቁር የግንባታ ወረቀት፤ የጸሃይ ብርሃን

አንድ ኩባያ በጥቁር ወረቀት ይሸፍኑት እና ሌላውን ባዶውን ይተዉት። ሁለቱንም ኩባያዎች በተመሳሳይ መጠን የሞቀ ውሃ ይሙሉ. ጎን ለጎን ቀጥታ የፀሐይ ብርሃን ላይ አስቀምጧቸው። ከ 10 ደቂቃዎች በኋላ, ኩባያዎቹን በመንካት ወይም ቴርሞሜትር በመጠቀም የውሃውን ሙቀት ያረጋግጡ። የትኛው ኩባያ የበለጠ ሙቀት እንደሚሰማው እና ለምን እንደሆነ ተወያዩበት። የጥቁር ኩባታው የፀሐይ ብርሃንን የበለጠ እንደሚስብ ያስረዱ, ይህም የፀሐይ ኃይል ነገሮችን እንዴት እንደሚያሞቅ ያሳያል።



## ተጨማሪ ሪሶርሶች (ADDITIONAL RESOURCES)



**ስለ የፀሐይ ኃይል ሌሎች መጽሐፍት**

- ዘ ማይቲ ሶላር ፓኔል 2022 (The Mighty Solar Panel (2022))
- ሶላር ስቶሪ፤ ሃው ዋን ኮሚኒቲ ላይቭስ አሎንግሳይድ ዘ ቢገስት ሶላር ፕላንት (Solar Story: How One Community Lives Alongside the Biggest Solar Plant (2020))
- ረኒንግ ኦን ሰንሻይን፤ ሃው ዳዝ ሶላር ኢነርጂ ዎርክ (Running on Sunshine: How Does Solar Energy Work? (2018))

©2025 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood